የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ

# ፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ

# FEDERAL NEGARIT GAZETTE

OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA

ሃያ ስድስተኛ ዓመት ቁጥር ፳፩
አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ
የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት ጠባቂነት የወጣ

26th Year No. 21
ADDIS ABABA 13th March, 2020

**ማውጫ**

አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፬/፪ሺ፲፪ ዓ.ም

በውጭ አገራት ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ……………………………………ገጽ ፲፪ሺ፪፻፷፰

**Content**

Proclamation No.1184/2020

The Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards RatificationProclamation…………Page 12268

## አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፬/፪ሺ፲፪

## በውጭ አገራት ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም ስምምነትን ለማጽደቅ የወጣ አዋጅ

በውጭ አገራት ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም ስምምነት ሰኔ ፫ ቀን ፲፱፻፶ ዓ.ም የወጣ በመሆኑ፤

ስምምነቱን ማጽደቅ ኢትዮጵያ የውጭ አገር ዜጎች የሚገቡበትን ውል በመፈፀም ያላትን መልካም ስምና ዝና በማሳደግ የውጭ ኢንቨስትመንት ፍሰት እንዲጨምር የሚያደርግ በመሆኑ፤

ይህንኑ ስምምነት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ የሕዝብ ተወካዮች ምክር ቤት የካቲት ፮ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም ባደረገው ስብሰባ ያፀደቀው በመሆኑ፤

በኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ ሕገ መንግሥት አንቀጽ ፶፭ (፩) እና (፲፪) መሰረት የሚከተለው ታውጇል፡፡

### ፩. አጭር ርዕስ

ይህ አዋጅ "በውጭ አገራት ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም ስምምነት ማጽደቂያ አዋጅ ቁጥር ፩ሺ፩፻፹፬/፪ሺ፲፪" ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

## PROCLAMATION No.1184 /2020

## A PROCLAMATION TO RATIFY THE CONVENTION ON RECOGNITION AND ENFORCEMENT OF FOREIGN ARBITRAL AWARDS

**WHEREAS,** the Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards was adopted on 10th June 1958;

**WHEREAS,** ratifying the convention enhances foreign investment by boosting a country's goodwill in enforcing contracts of foreign parties;

**WHEREAS**, the House of Peoples' Representatives of the Federal Democratic Republic of Ethiopia has ratified said Agreement at its session held on the 13th day of February 2020;

**NOW,THEREFORE,** in accordance with Article 55 (1) and (12) of the Constitution of the Federal Democratic Republic of Ethiopia, it is hereby proclaimed as follows.

### 1. Short Title

This Proclamation may be cited as "the Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards Ratification Proclamation No.1184/2020."

## ፪. መግለጫ

፩/ በስምምነቱ አንቀጽ ፩ (፫) መሰረት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ስምምነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው በሌላ የስምምነቱ አባል አገር ግዛት ውስጥ ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ብቻ ነው፡፡

፪/ በስምምነቱ አንቀጽ ፩ (፫) መሰረት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ መንግሥት ስምምነቱን ተግባራዊ የሚያደርገው በኢትዮጵያ ሕግ መሰረት ንግድ ለሆኑ በውል ወይም ከውል ውጭ ለሚፈጠሩ ግንኙነቶች ብቻ ነው፡፡

## ፫. ተዓቅቦ

ስምምነቱ የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክን በሚመለከት ተፈጻሚ የሚሆነው ስምምነቱ ተቀባይነት ካገኘበት ቀን በኋላ በተደረጉ የግልግል ዳኝነት ስምምነቶች እና የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች ላይ ብቻ ነው፡፡

## ፬. የስምምነቱ መጽደቅ

በውጭ አገራት ለተሰጡ የግልግል ዳኝነት ውሳኔዎች እውቅና የመስጠት እና የመፈጸም ስምምነት በዚህ አዋጅ ፀድቋል፡፡

## ፭. የጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ኃላፊነት

የፌደራል ጠቅላይ ዐቃቤ ሕግ ከውጭ ጉዳይ ሚኒስቴር እና ከሌሎች የመንግሥት አካላት ጋር በመተባበር ስምምነቱን የማስፈጸም ኃላፊነት በዚህ አዋጅ ተሰጥቶታል፡፡

## ፮. አዋጁ የሚፀናበት ጊዜ

ይህ አዋጅ በፌደራል ነጋሪት ጋዜጣ ታትሞ ከወጣበት ቀን ጀምሮ የፀና ይሆናል፡፡

**አዲስ አበባ መጋቢት ፬ ቀን ፪ሺ፲፪ ዓ.ም**

**ሳህለወርቅ ዘውዴ**

**የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲያዊ ሪፐብሊክ**

**ፕሬዚዳንት**

## 2. Declaration

1/ In accordance with Article 1 (3) of the Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia declares that it will apply the Convention for Recognition and Enforcement of Arbitral Awards made only in the Territory of another contracting State.

2/ In accordance with Article 1 (3) of the Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards, the Government of the Federal Democratic Republic of Ethiopia declares that it will apply the convention on differences arising out of legal relationships, whether contractual or not, which are considered commercial under the National Law of Ethiopia.

## 3. Reservation

The Convention only applies in the Federal Democratic Republic of Ethiopia with respect to Arbitration Agreements concluded and Arbitral Awards rendered after the date of its accession to the Convention.

## 4. Ratification of the Convention

The Convention on the Recognition and Enforcement of Foreign Arbitral Awards is hereby ratified.

## 5. Responsibility of the Attorney General

The Attorney General of the Federal Democratic Republic of Ethiopia is hereby authorized to undertake, in collaboration with the Ministry of Foreign Affairs and other Government Organs, all acts necessary for the implementation of the Convention.

## 6. Effective Date

This Proclamation shall come into force up on publication in the Federal Negarit Gazette.

**Done at Addis Ababa, this 13th day of March 2020**

**SAHLEWORK ZEWDE**

**PRESIDENT OF THE FEDERAL DEMOCRATIC REPUBLIC OF ETHIOPIA**